# <u>የመጨረሻው የሰራዊት ማፈግፈግ በጸለምት</u>

ጨዋታ ፈርሶ ወንዙም ደፍርሶ የውሃ ሙላት ደረሰና ያ ተራራ ይንዳል የተባለው ሰራዊት አንገቱን አቀርቅሮ ፤ የጠመንጃውን አፈሙዝ ደፍቶ ፤ አይኑ ቀልቶ ፤ ፊቱ ከስሞ ፤ የሀሳ-ብ ውጣ ውረድ እየታየበት የሚጉዋዝ የህልም ፈቺ ያለህ የሚል የመስላል ፣፣ በእውነቱ ጊዜው የጨለመና እንዲያ ካንተ በፊት እኔ ልሰዋ ይመካበት የነበረውን ጉዋዱን እየተጠራጠረ ፣ ነገ ምን ሊፈጠር ይሆን እያለ የሚቀባዝርበት  ወቅት ነበር ፣፣ በኤርትራ መሳሪያ ሊያመጣ የሄደ የሰራዊት ጦርና የህዝ-ብ አርበኛው ጸለምት በደረሰበት ጊዜ በአካባቢው የነበሩ የሰራዊትና የ-ብዙሃን ድርጁት አባላት በቡድንና በተናጠል ወደ ደርግና  ወያኔ የገቡበት፤ ዛሬ የምታዩትን ገዋድ/ጉዋዲት ነገ የማታይበት ፤ ሚስጥረኝነት እና ገዋደኝነት የሚን ጸባረቅበት፤ መሳሪያዬ ባርቃ እነዳትገድለኝ ተ-ብሎ የሚፈራበት የታሪክ ምእራፍ መታጠፊያ ፤ የህዝ-ብ ትጥቅ ትግል ፤ ሽምቅ ትግል  ጥቃት ጥበቃ ያከተመበት ታሪካዊ እውነታ ነበር ፤፤ ይባስ -ብሎ በደጋው አካባቢ የነበሩ ወላዋይ ጸረ ትግል የነበሩ አርሶ አደሮች ጭርሽኑ ጠቅልለው ወደ ደርግ ሲገቡ የደርግ አዋጊዎች ደግሞ እነሱኑ መሪና ተዋጊ አድርጎ በሚያውቁት ተራራና ገደል የጠላትን ወታደር እያዘገሙ ይዘውት መግባት ጀምሩ፤፤ ይህ አልበቃ -ብሎ  በደጋው ጦርነት እየተደረገ መጨረሻ ለይ የተሰዉትን የሰራዊት አባለት ማስታወስ አስፈላጊ ነው -ብዬ አምናለሁ፤፤ በእርገጥ የሃሳ-ብ ልዩነት ቢኖርም በዚያች  የመጨረሻ ቀን መስዋእት መሆን ግን ፍጹም እምነት ነው ፤፤ እነኚህ ጉዋዶች ከጦርነቱ በሁዋላ ጸለምትን ለቀን እነደምንወጣ ያውቁ ነበር ፤፤ ግን ለምን? ይህንን ለእናንተው ልተወው እና ወደ መጨረሻው ማፈግፈግ ወይንም ጥሎ መውጣት ልውሰዳችሁ፤፤

ወቅቱ መራራው ሀሩር አልፎ የዝናቡ ጊዜ እየደረሰ፤ ጸሃይ ደህና ሁኑ -ብላ የምታውለበል-በበትና ፤ ዝና-ብና ደመና የነገሱበት ይመስላል ፤፤ ከደጋውና ዙሪያው እነዲሁም ከተለያየ ቦታ ያሉ ጉዋዶች በተናጠልና በቡድን ከመጣደፉ የተናሳ ቁስለኛው ኡኡ እያለ እና አባካችሁ አሳርፉኝ ወይም ጨርሱኝ -ብሎ እየተማጸነ ፤ በሩጫ ጸሀይ ገባች እሩጥ ሆነና ፤ ሁሉም ደኑን ጥሶ ቆንጥሩን ዘሎ ትርምስ የበዛበት ያልተቀናጀ እግሬን አውጪኝ ይመስል ነበር፤፤
በመሰረቱ የአመራሩ ክፍሉም ቢሆን የትኛው አ-ብሮ የሚሄድና ያመራሩን ትእዛዝ ሊቀበል የሚችል ጉዋድ ለማወቅ በጣም አስቸግሮት ነበር፤፤ ዛሬ የምታየውን ነገ ይመስል ነበር ፤ ሴትና ወንዱ እጁ ለእጁ ተያይዞ በ-በሄረ ጽጌ ወይም በባህር ዳር ንፋስ ለመቀበል የወጡ  ትኩስ ፍቅረኞች ይመስሉ ነበር፤፤  በአመራር አካባቢ ያለው ደግሞ ዶሮና በግ እያረደ ሲመገ-በ እና ሲፍነሰነስ ፤ ዋ ይህም አለ ለካ በማለት የተገረምነው -በዙዎቻችን ሳንሆን አንቀርም፤፤
ይህ በዚህ እንዳለ ጠላት በደጋውም ሆነ በቆላው የሰራዊቱን መበታተን በማየት አሰሳውን ቀጠለ፤፤ የሰራዊቱ አመራርም በሉ አሁኑኑ መጉዋዝ አለ -ብን -ብሎ ትእዛዝ ሲሰጥ ወደ ወያኔ የሚሄደው ወደ ትግራይ ሲገባ ፤ ወደ

ደርግ የሚገባው ደግሞ አድርቃይ እጃቸውን ሰጡ ፤ ፍጹም ነው እምነቴ ያልነው አመራሩን ተከትለን፣ ተራራውን ቡዋጥጠን፣ ደኑን ጥሰን ፣ ቆንጥር ለቆንጥር ተጉዘን በደጋው አካባቢ የነበሩ ህዝባዊ አርበኞች ከአርትራ የመጣውን G3 ታጥቀው ለ-በቻቸው ከጠላት ጋር የተፋለሙበት ነበር፤፤ይህ ሰራዊት ከመደበኛው ሰራዊት ባላነሰ የተዋጋና የተዋደቀ፣ ን -በረቱንና ፣ ሚስቱን እና ልጆቹን ጥሎ ትግሉ ትግሌ ነው በማለት በቆራጥነት የሚዋደቅ ክፍል ነበር፤፤ ኤርትራ መሳሪያ ለማምጣት በሄድን ጊዜ አ-በረውን ተጉዘው ከወያኔ ጋር መግእ ላይ ስንፋለም አ-በረወን የተፋለሙና የሞቱ ህዝባዊ ስሜትና አ-በዮታዊ ወኔ የነበራቸው አርበኞች ነበሩ ፤፤ በመጨረሻው ጉዞ ላይ ሊወጉን የችላሉ ተ-በለው የተፈሩትም በቆላውም ሆነ በደጋው ያሉት ህዝባዊ አርበኞች ነበሩ፤፤ ከሁሉም የማነረሳው ነገር ቢኖር እንደዚያ ተያይዘን በፍጥነት ስንጉወዝ ባላገሩ እየተከተለ ጉወዶች ወዴት ነው የምትሄዱት እኛ እኮ ምንጊዜም ከናተ ጋር ነን፤ ፤ አገሮቻችን ፣ አስተማሪዎቻችን ናችሁ፤፤ አገዳደልና አሙዋማትን አስተምራችሁን፤ ዛሬ እንዴት ጥላችሁን ለአረመኔው የደርግ ጦር አጋልጣችሁን ለጥን-ብ አሞራ ትሰጡን? እያሉ ሲሉ በከተማው በየስውር ቦታው መውጫ እስከምናገኝላችሁ ቆዩ -በለን በተስፋቀ የተውናቸውንና በጠላት ወድቀው ለዘመናትንና ፍጹም ነው እምነቴን እየዘመሩ የወደቁት ሰማእታት ትዝ ይሉኛል፤፤ በጸለምት ቆላ የነበሩት ወንድ ሴት ፤ ወጣት ፤ ጎልማሳ ሳይቀር ሲላቀስ ፣ ግማሹ ደግሞ በንዴት ተወጥሮ አይኑ ቀልቶ የሚታየው -በዙ ነበር፤፤ ጉልበታቸው ደክሞ አቅም አጥተው የት እን ደደረሱ ያልታወቁት እነ ጉዋድ ሰለሞንን (ግርማቸው አበበ) ማስታወስና መጥቀስ እፈልጋለሁ፣፣ ይህንን ደግሞ አመራሩና በዙሪያው የነበሩ መመለስ ይችላሉ፤፤

ጸለምትን በፍጥነት ለቀን ስንወጣ ወልቃይትን ደግሞ በሩጫ ሸምጥጠን በሽተኛውንና ቁስለኛው እየጮሀ ጉልበተኛው እየሸለለ ፤ ደካማው በሲቃ እያማለለ ተከዜን አቁዋርጠን እረፉ ተባለ፤፤ የምግ-ብ ጉዳይ እንኩዋን ለደህናው ለበሽተኛውም መልስ አልነበረውም፤፤ በድካም ላይ ከወንዙ ውሃ ጠጥተን ቁጭ እንዳልን ሁለት የሰራዊት አባላት እጃቸውን የፊጥኝ ወደ ሁዋላ ታስረው ወደ ፊት በቲም ስኩዋድ ታጁበው ሰራዊቱ ፊት ሁለቱም ተረሸነዋል፤ ተገድለዋል፤፤ ለሁላችንም በጣም አስገራሚ ነገር ነበር፤፤ በሁዋላ ምክንያቱን ስንጠይቅ መሳሪያ ይዘው ሲከዱ ተይዘው ነው ተባልንና ስንቱን መሳሪያ አስጥልነው ነው? እነኚህ የጸለምት (የዲማ) ወጣቶች ላይ እንዴት ነው -በረታችን የበረታው እያልን አንገታችንን ደፍተን ተቀበልነው፤፤ ይህ በእንደዚህ እያለ ተነሱ ተ-በለን ወዲያው ወደ ማህል የጆ-በሀ ግዛት ገ-በተን አደርን፤፤ በበነጋው በጆ-በሃ ሚልሻያ የተከበበች በድንጋይ አለትና በአሸዋ የተሞላች ፤ በዛፎች በአበበች ቦታ ላይ እረፉ ቦታ ያዙ ተ-በሎ ሰራዊቱ በዙሪያ አመራሩ መካከል ላይ በመሆን ሰፈርን፤፤ በዚህች በተራራ በተከበበች ቦታ ላይ ለግዞት እንደተቀመጠ እስረኛ ሌት ተቀን የሰማይ አድማስ እያየን፤ እንደዚያ ይወናጨፍ የነበረው እግራችን

ታስሮ ፤ የትግል ረሃ-በተኛው እንደበታችንና ወኔአችን ተሰ-በሮ ይናገር የነበረው ድምጻችን ተቆልፎ ፤ ሰውነታችን በበረሃው ሙቀት ደክሞ ፤ ሾቆ ከሰነበትን በሁዋላ ታሪካችንን እንደገና እንመርምር በማለት በጠቅላይ አመራሩ (የፓርቲው አመራር) የሚካሄድ ለአስራምስት ቀን ያህል ውይይቱ ቀለጠ፤፤

አመራሩም ከዚህ ውይይት በተነሳ አዲስ ህቡእ የፓርቲ አባላት ተመርጠው በየጋንታው ተሰግስገው በህቡእ እየተገናኙ ሁሉን የሰራዊት አባል እየገመገሙ ለአመራር ያቀርቡ ነበር፤ የአስራ አምስቱ ቀን ግምገማ አወዛጋቢና አጨቃጫቂ ከመሆኑም አልፎ አሰልች እና አድካሚም ነበር፤፤ አመራሩ በስ-በሰባው ላይ የተካፈለውን ሁሉ በአንክሮ እየተመለከተ ማን ከኛ ጋር የሄዳል፤ እነማንስ የበታኞች ተከታይ ናቸው እያለ ኢላማ ውስጥ ማስገባት ጀመሩ፤፤ ውይይቱ ካበቃ ሳምንት ሳይሞላው አስቸኩዋይ አጠቃላይ ስ-በሰባ በማለት ወደ ምሽት አካባቢ ተጠራንና በተመለመሉ ታጣቂዎች ተከበን ስ-በሰባው በፓርቲው አመራር ተጀመረ፤፤ ወዲያውኑ የስ-በሰባው እንደምታ ተቀየረና አሁንም የሚበጠ-በጡን ከዚህ በፊትም ሲበጠ-በጡን የነበሩና የከሃዲዎችና የበታኞች ርዝራዞች ከመካከላችን ትናትና ማታ ከድተዋል፤፤ ከመሃላችንም የእነሱ ጉዋዶች እና አቀንቃኞች ስላሉ ተይዘው በቁጥጥር ውስጥ መዋል አለባቸው -በለው ሃሳ-በ ስጡበት ሲሉ አንዱ የሃይል አመራር አባል ፣- የሚታሰረውን ማሰር ፤ የሚገደለውን መግደል ነው -በሎ እንዳበቃ፤ የተጠረጠሩ ጉዋዶች ስም መዘርዘር ተጀመረ፤፤ አስራ ሁለት ያህል ጠሩና ቆም እነደማድረግ አድርገው እንደገና የሁለተኛው ዙር ስም ዝርዝር መጥራት ጀመሩ፤፤ አንድ ጉዋድ በሚጠራበት ጊዜ አመራሮች ፊት የቀር-በና መሳሪያና ትጥቅ ያወርዳል፤ በልዩ ታጣቂዎች በተከበበች ቦታ ላይ ስ-በሰባው እስከሚያልቅ በጊዜያዊ ይቀመጣል፤፤ ስም መጥራቱ እን ደቀጠለ አንዱን ጉዋድ -በረት አውርድ ሲሉት አቀባበለና ሁለቱን የሃይል መሪዎች ሲገድል ሶስተኛውን አቆሰለና እሱም ተገደለ፤፤ የሞቱት የሀይል አመራሮች ስበርና በርሄ ሲሆኑ የቆሰለው ደግሞ ሀዲሽ (ሪጂን 4 አመራር የነበረው ) ነው፤፤ ተኩሱ እነደ ቀለጠ መሳሪያ ያወረዱትን ጉዋዶች በቀጥጥር ላይ ያሉትን ጊዜያዊ እስረኞች በሉአቸው የሚል ድምጽ ተሰማ ፤ በዚየአን ጊዜ የሚሮጠው ሮጦ አመለጠ፤፤ የተቀረው ግን ተይዞ ለ-በዙ ጊዜ ታስረው የሰውነትና የአእምሮ ስቃይ አሰቃይተው አሰና-በተዋቸዋል ፤፤

ይህ ጹህፍ ለወደፊቱ ቀጣይነት ይኖረዋል፤፤ በዚህ ላይ ጥያቄ፣ ወይም አስተያየት ካላችሁ በደሲታ እቀበላለሁ፤፤